# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 319 ሰኔ 13 2006 ገጽ 1


ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ለመላው ሕዝባችንና በተለይም ለወጣቱ ትውልድ በተደጋጋሚ እንደሚለው የሀገራችን ባለቤት ለመሆን የምናደርገውን ትግል ተቀላቀሉ!!! መቀላቀል ያልቻላችሁም በኣካባቢያችሁ ከምታምኗቸው ወገኖቻችሁ ጋር ተሰባሰቡ፣ በህዋስ ተደራጁ። ግንቦት 7 በዚህ ትግል የዳር ተመልካች ሳይሆን መሪ እንድትሆኑ ኣገራዊ ጥሪውን ያቀርባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ጥናት ኢትዮጵያ ከአለማችን ደሃ አገሮች አንዷ መሆኗን እንደገና አረጋገጠ

Multidimensional Poverty Index በምህፃረ ቃሉ (MPI) የተባለውና የዓለማችንን 108 ሀገራት የድህነት ደረጃ የፈተሸው የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ጥናት ይፋ ያደረገው መረጃ እንዳመለከተው ኢትዮጵያ ከ108ቱ ሀገራት ኒጀርን ብቻ በልጣ ከመጨረሻቹ በሁለተኛ ደረጃ ማለትም 107ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል። ጥናቱ በኢትዮጵያ ከጠቅላላው ህዝብ 76 ሚሊዮኑ እጅግ በከፋ ድህነት የሚማቅቅ መሆኑን አመልክቷል።

ደረጃው በትምህርት፣ ጤና እና የኑሮ ሁኔታ ላይ የሚያጠነጥኑ 10 መስፈርቶች ሲኖሩት ከ10ሩ መስፈርቶች አንድ ሦስተኛውን እንኳ ያላገኘን አገር ዘርፈ ብዙ ደሃ (Multi- dimensionally poor) በማለት ሲፈርጅ፣ ከመስፈርቱ ዝርዝር ውስጥ አንድ ሦስተኛ ያህል የተሟላለትን አገር ደግሞ ለኑሮ መሰረታዊው ነገር ያልተሟሉለት (Destitute) በማለት አስቀምጧል። በዚህም መሰረት ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ህዝብ 87.3% ያህሉ ዘርፈ ብዙ ደሃ በሚለው ክልል ውስጥ እንደሚገኝና 58.1% ቱ ደግሞ መሰረታዊ ነገር ያልተሟሉለት (Destitute) በሚለው ክልል ውስጥ እንደሚገኝ የጥናት ውጤቱ ያሳያል።

የገጠሪቱን ኢትዮጵያ በተመለከተ ጥናቱ 96.3% የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ በከፋ የድህነት አረንቋ ውስጥ እንደሚገኝ ሲገልጽ በአንጻሩ ከከተማ ነዋሪው 46.4 % ቱ በከፋ ድህነት ውስጥ እንዳለ ተመልክቷል። በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች የሚስተዋለውን የድህነት ደረጃ አስመልክቶ ጥናቱ ይፋ ያደረገው መረጃ እንዳመለከተው በየክልሉቹ ከጠቅላላው ህዝብ በሶማሌ 93%፤ በኦሮሚያ 91.2%፤ በአፋር 90.9 %፤ በአማራ 90.1 %፤ በትግራይ 85.4 % ህዝብ በድህነት አረንቋ ውስጥ እንዳለ ይገልጻል።

## የወያኔ ቤት አፍራሽ ግብረ ሃይል ላፍቶን ካለቤት የማስቀረት ዘመቻዉን ተያይዞታል

የጉጅሌው ወያኔ ቤት አፍራሽ ግብረ ሃይል በነፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ ቃሬሳና ኮንቶማ ሰፈር ወደ 5000 የሚጠጉ ህጋዊ ቤቶችን ለማፈራረስ እንቅስቃሴ መጀመሩን ተከትሎ ከ 3000 በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች መድረሻ አጣን በማለት በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጽ/ ቤት ደጃፍ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው ታወቀ። ነዋሪዎቹ ካለምንም ተተኪ ቦታ መድረሻ አታሳጡን በማለት በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ቢገልፁም ሰሚ ማጣታቸውን ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። የአካባቢው ወጣቶች ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ በሚል ስጋት ወስጥ የወደቀው ህወሓት መራሹ ወያኔ በቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶቹ አማካኝነት ወጣቶችን በቆመጥ እየደበደቡ ከአካባቢው ማባረራቸውንም ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው ያለው ውጥረት አሁንም ድረስ እንደቀጠለ መሆኑም ታውቋል።

የፋሽስቱ ወያኔ ቤት አፍራሽ ግብረ ሃይል በአዲስ አበባ ብቻ በብዙ ሽዎች የሚቆጠሩ ህጋዊ ቤቶችን በማፈራረስ ነዋሪዎችን ለጎዳና ህይወት እየዳረገ እንደሚገኝና እየተከታተልን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን በቅርቡም ቤታቸው በመፍረሱ መግቢያ ያጡ የአራት ልጆች አባት ዳስ ጥለው ኑሮዋቸውን ከሚገፉበት ቦታ በጅብ ተበልተው መሞታቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

በሌላ ዜና የነፍሰ በላው ወያኔ ቅጥረኛ ካድሬዎች በምስራቅ ጎጃም ዞን *በነማይ ወረዳ ደንጎሊማ* ቀበሌ አቶ ሞሳ አዳነ የተባሉትን የመኢአድ አባል ደብድበው መግደላቸው ታወቀ። ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለት ቅጥረኛ የብአዴን ካድሬዎች ማንነታቸው የታወቀ ሲሆን ገዳዮቹ ወደ ሟች መኖሪያ ቤት በመሄድ ወደ እስር ቤት ትሄዳህ በማለት ለማስገደድ ሲሞክሩ በተፈጠረ አለመግባባት ካድሬዎቹ በፈጸሙበት ከፍተኛ ድብደባ ወዲያውኑ ሕይወቱ ማለፉ ተዘግቧል።

ግዜ

## የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎች የፍትህ ያለህ ብለዉ ጩኸታቸዉን እንደቀጠሉ ነዉ

በምስራቅ ጎጃም ዞን የደብረ ማርቆስ ከተማ ኗሪዎች የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ሹማምንት በሚያደርሱባቸው በደሎች ክፉኛ መማረራቸውን የአካባቢው ዘጋቢያችን ያደረስን መረጃ ያመለክታል። ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎች እንደገለጹት በጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት ትዕዛዝ በአደባባይ እንደበደባለን፤ እንታሰራለን፤ እንገደላለን፤ ቤቶቻችን ይፈርሳሉ፤ በአገራችን በሰላም ለመኖር አልቻልንም ሲሉ በአገዛዙና ሹማምንቱ ላይ ያላቸውን ምሬት አሰምተዋል። በተደጋማሚ በሚደርስባቸው በደል አገር ጥለው የሚሰደዱ ዜጎች መበራከታቸውንም ነዋሪዎቹ ገልጸዋል።

በዞኑ ብሎም በከተማዋ ሹመት የሚሰጠው በዘመድ አዝማድ ነው ያሉት አንድ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የአካባቢው ነዋሪ፣ ድርጊቱን በሚቃወሙት ላይ ደግሞ እርምጃ እንደሚወሰድባቸው ተናግረዋል። ሌላኛው የደብረ ማርቆስ ነዋሪ እንደገለፁት በዘመድ የተሾመ የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት እና በ15 ቁጥር ምስማር የተመታ እንጨት አንድ ናቸው፣ ሁለቱም አንዴ ከገቡ ለመንቀል ያስቸግራሉ ካሉ በሁዋላ፣ ክፉ የሚሰራው በፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት ተመርጦና ተወዶ ይሾማል፣ ደጉና ለህዝብ ቅን አሳቢው ደግሞ ይወረዳል ሲሉ በአገዛዙ ሹመት ላይ ያላቸውን ትችት ሰንዝረዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ዞን 9ኞች እንደገና ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ተሰጣቸዉ

በፌስ ቡክ እና ብሎግ የተለያዩ ጽሁፎችን በመጻፍ በወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ደጋፍ ያገኙት ዞን 9 እየተባሉ የሚጠሩ ወጣት ጸሃፊዎችና ጋዜጠኞች ባለፈው ቅዳሜ በወያኔው ካንጋሮ ፍርድ ቤት ቢቀርቡም፣ 28 ቀናት የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸው ወደ ማእከላዊ እስር ቤት መመለሳቸው ታውቋል። እጆቻቸውን በካቴናዎች የታሰሩት ወጣት ብእረኞች አካላዊ መጎሳቆል ቢታይባቸውም፣ መንፈሳቸው ግን ጠንካራ መሆኑን ዘጋቢያችን ከላከልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

ችሎቱን ለመከታተል ከ 400 በላይ የሚሆን ህብረተሰብ በፍርድ ቤቱ ደጃፍ መገኘታቸውን ያደረሰን ዘጋቢያችን ጦማርያኑና ጋዜጠኞች በፈገግታ የተሰበሰበውን ሰው ሰላም እያሉ ሲያልፉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በፍርድ ቤቱ አካባቢ የተሰበሰበው ህብረተሰብም በእጅ ሰላምታና ድጋፍ ሲሰጧቸው የነበረ ሲሆን ችሎቱን ለመመልከት ያመሩ በርካታ እናቶችና ሴቶች ሲያለቅሱ ተስተውለዋል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በፌስ ቡክ እና በተለያዩ የማህበራዊ የመገናኛ መንገዶች የሚሰራጩ መረጃዎችን ለማዛባትና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ባጀት መድቦ በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆን በቅርቡም በአገዛዙ ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደ ስራ የገቡ ከ 200 በላይ ግለሰቦች መኖራቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## የአዳዲሶቹ የስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ መጓተቱትን መረጃዎች አመለከቱ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ ታሪካዊ ገዳም እያፈረሰ ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ ደግሞ ነፃ አወጣኋችሁ የሚላቸዉን ብሄር ብሄረሰቦችን ከመሬታቸዉ ላይ በግድ እያፈናቀለ የጀመራቸዉ አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎች ፕሮጀክቶች የተጓተቱ መሆኑን ከወያኔዉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ጠቆመ። የሚኒስተር መ/ቤቱ የስራውን ስፋትና ዉስብስብነት አንደ ዋና የአፈጻጸም ጉድለት ወይም መጓተት ምክንያት አድርጎ ቢያቀርበዉም እንደ ብዙ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ኤክስፐርቶች እምነት የቅድመ ፕሮጀክት ጥናት ደካማነት፤ የመሰረተ ልማት ግንባታ አለመኖር፤ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል እጥረትና ፕሮጀክቶቹን ለመጀመር ሲባል ከመሬታቸዉ የተፈናቀሉ ገበሬዎች የፈጠሩት አለመረጋጋት የችግሩ ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዉያን ደሃ ገበሬዎችን ከመሬታቸዉ ላይ አባርሮ የስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክቶችን ከጀመረ አመታት የተቆጠሩ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ባለዉ ዉጤት ግን ከፕሮጀክቶቹ በፊት ታስቦ መሰራት የነበረባቸዉን የመሰረተ ልማስ ስራዎች ከመስራትና ፋብሪካዎቹ ይተከላሉ በተባለባቸዉ ቦታዎች መኖሪያ ቤቶችን ከመስራት አልፎ የአገሪቱን የስኳር ችግር የሚፈታ ምንም ነገር አለመደረጉን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህም መሰረት ምኩራዝ፣ጣና በለስና ወልቃይት የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ የተባሉ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ቀና ብለን የምንሄድበት ጊዜ አየመጣ ነው! ጎበዝ ተነሳ!

ጉጅሌዎቹ አይገባቸውም እንጂ የኢትዮጵያ ከተሞችና ገጠሮች የለውጥን ደመና ኣርግዘዋል። ወንዞችም ተራሮችም የለውጥ ማዕበል ማቆብቆቡን አያበሰሩ ናቸው። የቀደሙት ገዢዎች መረጃ የሚያገኙት እረኛ ምን ይላል ብለዉ እየጠየቁ ነበር። የአሁኖቹ አገር አጥፊ ገዢዎች ምሳሌ ያደረጉት ካድሬዎቻቸውን ብቻ ሆነ እንጂ ዛሬም የአገራችን እረኞች የለውጥን መምጣት በሚያምር ቅላጽያቸው አያንጎራጎሩ እንዲህ አያሉን ነው፣

የሀገሬ ጉብል የሰማውን እንጃ
የጎንደሬው ጉብል የሰማውን እንጃ
ከብቱን አየሸጠ ገዛ ኣሉ ጠብመንጃ።
የወሊጋው ጉብል የሰማውን እንጃ
ቡናውን ሻሽጦ ገዛ ኣሉ ጠብመንጃ።

መልእክቱ ግልጽ ነው። የኢትዮጵያ ወጣቶች አገራቸውን በክቡር ደማቸው ሊታደጓት ቆርጠው በመነሳት ወያኔን በማስወገድ የሀገራቸው ባለቤት ለመሆንና ያልተከፋፈለች ውብ ኢትዮጵያን ማየትን ለማረጋገጥ ጥርጊያውን መጀመራቸው ነው።

ላለፉት ፵ አመታት አምባገነኖች ባደረሱብን ጭቆና እና እንግልት የተነሳ የራሳችን የሆነ መንግሥት ሳይኖረን አንገታችንን ደፍተን ጀግኖቻችንን ስንገብር ኖረናል። በተለይም ባለፉት ፳፫ አመታት ጉጅሌዎቹ በአራት ኪሎ ከነገቡን ጀምሮ በአንድ ላይ አንዳንቆም በማድረግና እና አርስ በራሳችን በማጋጨት ሲያባሉን ኖረዋል።

ዛሬ ሁኔታዎች ተለውጠዋል፤ በውጭም በአገር ውስጥም ለውጥ አየታየ ነው። የእንቅስቃሴው ማእበል አይሎ እየመጣ ነው። ዛሬ ሁሉም የዴሞክራሲ ሀይሎች ማለት በሚቻል ደረጃ በሁለት ነገሮች ላይ ስምምነት አለ፣

፩. ተቃዋሚዎች በግል ከሚያደርጉት ትግል ይልቅ በጋራ የመሰባሰብን አስፈላጊነት ተረድትው መሰባሰብ መጀመራቸው

፪. በአንድ ላይ መሰባሰብ ካልቻሉም እርስ በራስ ላለመጠላለፍ መስማማት መቻላቸውና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ግዜ ሁሉ መረዳዳት መጀመራቸውና በግልም ከወያኔ ጋር የሚደረገውን ትግል ማፋፋም የቻሉበት ሁኔታ አየታየ መሆኑ የሕዝብ ወገኖችን እያስደሰተ ይገኛል።

በአገር ቤት የሚገኙ የዴሞክራሲ ኃይሎችም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሕዝቡ ከፍርሀት ተላቆ ለመብቱ እንዲነሳ የሚያደርጓቸው አንቅስቃሴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከሩ መጥተዋል። ለዚህም በቅርቡ በአዲስ ኣበባ መድረክ፣ ኣንድነትና ሰማያዊ ፓርቲዎች የጠሯቸው ሰልፎች ይበል የሚያስብሉ ናቸው።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በዚህ ኣጋጣሚ ለዴሞክራሲና ለነፃነት ታጋዮች ሁሉ ያለውን አክብሮትና ኣድናቆት ይገልጻል።
በሌላም በተለያዩ አቅጣጫዎች ወያኔን በኣመጽ ለመፋለም የወሰኑ ኃይሎች ከመቼውም ጊዜ በላይ ወያኔን ለመፋለም ቆርጠው በጋራ ክንዳቸውን ኣቀናጅተው ለመፋለም አየተዘጋጁ ያሉበት ሁኔታ አበራታች ነው። እነዚህ ኃይሎች አዳዲስ የነጻነት ታጋይ አርበኞችን በተከታታይ በማስመረቅ ያሉ መሆናቸውና ከዚህም በተጨማሪ ከመላው የአገሪቱ አካባቢዎች ወጣቶች በገፍ ትግሉን እየተቀላቀሉ መሆኑን ስንሰማ ልባችን በደስታ ይሞላል።

በወያኔ ጉያ ውስጥ ያሉ የሕዝብ ወገኖች ደግሞ የቻሉትን በውስጥ ሆነው መቃብሩን እይቆፈሩለት ሲሆን፣ ያልቻሉትም የወያኔን ሚስጢር ይዘው በመውጣት የሕዝብ ወገንተኝነታቸውን አየገለጹ ይገኛሉ።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ለመላው ሕዝባችንና በተለይም ለወጣቱ ትውልድ በተደጋጋሚ እንደሚለው የሀገራችን ባለቤት ለመሆን የምናደርገውን ትግል ተቀላቀሉ!!! መቀላቀል ያልቻላችሁም በኣካባቢያችሁ ከምታምኗቸው ወገኖቻችሁ ጋር ተሰባሰቡ፣ በህዋስ ተደራጁ። ግንቦት 7 በዚህ ትግል የዳር ተመልካች ሳይሆን መሪ እንድትሆኑ ኣገራዊ ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የቤንሻንጉል ጉሙዝ ተፈናቃዮች የደረሰባቸዉ በደል ለክስ አያበቃም አለ

የወያኔዉ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ባለፈዉ ዓመት ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የተፈናቀሉ ዜጎች የደረሰባቸዉ በደልና ሰብዓዊ መብታቸዉ መደፈር ለክስ የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም በማለት ወያኔ የዜጎችን መብት እንዳሰኘዉ መርገጥ የሚችል መሆኑን አረጋገጠ። ተፈናቃዮቹ በተወካዮቻቸው አማካኝነት የመሰረቱት ክስ በፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት 8ኛ ፍትሃ ብሄር ምድብ በዋለው ችሎት የታየ ሲሆን ፣ በቀረበው ክስ ላይ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴርና የቤንሻንጉል ክልል መንግስት መልስ ሰጥተዋል።

ከሳሾች ለበርካታ አመታት ከኖሩበት መንደር በህገወጥ መንገድ መፈናቀላቸውንና ሃብትና ንብረታቸውን ማጣታቸውን በጠበቃቸው አማካኝነት ተናግረዋል። ሆነም ለዜጎች መብት መከበር ጥብቅና መቆም የነበረበት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ከሳሾቹ ቤት ንብረት አለማፍራታቸውን ጠቅሶ፣ ከሳሾቹ ምንም ለክስ የሚያበቃ ነገር ሳይኖራቸው ጉዳያቸው ለፖለቲካ ፍጆታነት እየዋለ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል።

ኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥንና ሬድዮ በጉዳዩ ዙሪያ ላይ ያናገራቸው ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማርያም የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ‘ጉዳዩ የሚመለከተው የክልሉን መንግስት እንጅ የፌደራሉን አይደለም’ በማለት የሰጠው መልስ ትክክል አለመሆኑን ተናግረዉ የህገመንግስቱ አንቀጽ 52 ማንኛውም የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲፈጸም የፌደራል መንግስቱን እንደሚያገባው፣ በዚህም የተነሳ የፌደራል መንግስቱ አይመለከተኝም ማለት እንደማይችል ገልጸዋል። ባለፈዉ ዓመት የአማራ ተወላጅ የሆኑ ዜጎች ከከቤኒሻንጉል ጉምዝ የመባረራቸዉ ዜና የአገሪቱ የመወያያ ዜና መሆን ሲጀምር ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ ‘ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ሰዎች እንዲፈናቀሉ ያደረጉትን ለፍርድ እናቀርባለን’ ብሎ መናገሩ የሚታወስ ነዉ።

## የጋዝጊብላ ነዋሪዎች ወያኔ አይክዱ ክህደት ካደን ሲሉ ማማረራቸዉ ተሰማ

በአማራ ክልል ከሰቆጣ ከተማ ጥቅት ኪሎሜትሮች ወጣ ብላ በምትገኘዉ ጋዝጊብላ ወረዳ የሚኖሩ የቀድሞ የወያኔ ታጋዮች ከትግራይ ህዝብ በመቀጠል ለወያኔ ወደ ስልጣን መምጣት ከፍተኛዉን የህይወት መስዋትነት የከፈልነው እኛ የሰቆጣና አካባቢዋ ነዋሪዎች ቢንሆንም፣ ወያኔ አዲስ አበባን ከረገጠ በኋላ ግን ዬት ገቡ ብሎ ጠይቆ እንደማያዉቅ ገለጹ። እነዚሁ በጋዝጊብላ ወረዳ የሚኖሩ የቀድሞ ታጋዮች ለኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥንና ሬድዮ እንደገለጹት፣ በመካከላችን ለወያኔ ልጁን ያልገበረ ሰው የለም ሆኖም ሌሎች ለወያኔ የታገሉ ኃይሎች የዉጊያ ዘመን ቆያታቸዉ እንደ አገልግሎት ዘመን ሲታሰብላቸዉ አንዳንዶቹም ቱጃር የመሆን በር ተከፍቶላቸዉ ኃብት ሲያከማቹ እኛ ግን እንደ ቆሻሻ ዕቃ ተጥለን ተረስተናል ሲሉ አማርረዋል።
ከሰቆጣ ላሊበላ የህዝብ ትራንስፖርት አለመኖሩን፣ ከአዲስ አበባ ሰቆጣ ደግሞ አገር አቋራጭ አውቶቡሶች ያልተመደቡ መሆናቸውን የሚገልጹት ነዋሪዎች ከአዲስ አበባ ሰቆጣ ለመድረስ ደሴ ከተማ ላይ እስከ 4 ቀናት መጠበቅ ግድ እንደሚላቸው ተናግረዋል። ከ 17 አመታት በፊት የተጀመረው ከአለም ከተማ ወደ ላሊበላ የሚወስደው መንገድም በአየር ላይ መቅረቱን ገልጸዋል። ህዝቡ ተቃውሞ ሲያሰማ “ዛሬ ነገ ይሰራል” በማለት እንደሚደልሉት የሚናገሩት ነዋሪዎች፣ መንግስት ለጥያቄያቸው መልስ ከመስጠት ይልቅ ህዝቡን መከፋፋል መምረጡን ገልጸዋል። አቶ በረከት ስምኦንና ሌሎች ባለስልጣኖች ሲመጡ የህዝቡን ችግር ሰምተው እንዳልሰሙ ሆነው እንደሚያልፉት ነዋሪዎች ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ከዋግ ህዝብ ትምህርት ይውሰድ የሚሉት ነዋሪዎች፣ በተለይ የድሮ ታጋዮች በረንዳ ላይ መውደቃቸውንና የሚሰማቸው ማጣታቸውን ገልጸዋል።

---

## የአዳዲሶቹ የስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ መጓተቱትን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አዳዲሶቹ ስኳር ፋብሪካዎች የፋብሪካና የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች እየተከናወኑ ቢሆንም አፈጻጸማቸው ግን አጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መሆኑን ከወያኔ ከራሱ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። የወያኔ አገዛዝ ምንም አይነት ቅድመ ዝግጅት ሳያደርግን ቅድመ ጥናት ሳያካሄድ ብዙ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በማቋረጥ ይህ ነዉ ተብሎ ሊነገር የማይችል የአገሪቱን ጥሪት እንደሚያባክን በተደጋጋሚ የተነገረ ሃቅ ነዉ። ለምሳሌ በአንድ ወቅት የስኳር ኮርፖሬሽን ዳይሬክተር የነበረዉ አባይ ጸሐዬ የስኳር ፋብሪካዎቹ በዘርፉ ልምድ ባለመኖሩ ምክንያት የማስፈጸም አቅም ማጋጠሙን አምኖ “እየተማርን በመስራት ላይ ነን”ብሎ ለፓርላማዉ መናገሩ የሚታወስ ነዉ። ወያኔ የተማረዉንና ልምድ ያለዉን ኢትዮጵያዊ በራሱ ካድሬዎችና ከጦር ሜዳ በመጡ ታጋዮች እየተካ ነዉ ነዉ እንጂ ኢትዮጵያ በስኳር ምርት ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ልምድ ያለዉ ሰራተኛና ኤክስፐርት ያካበተች አገር ናት።

## የመጨረሻዉ መጀመሪያ

በቅርቡ በተከታታይ አገር ቤት ዉስጥ ቅርጽና ይዘት እየያዙ የምናያቸዉና ማንም አሌ የማይላቸዉ ግዙፍ እዉነታዎች ሁሉም በአንድነት የሚጠቁሙት አይቀሬዉ የወያኔ መጨረሻ መጀመሩን ነዉ። ከዚህ ቀደም በግልጽ እንዳየነዉ ወያኔ አንድ ቦታ ሲሸነፍ ሌላ ቦታ እያሸነፈ በጉልበትም በተንኮልም የፖለቲካ የበላይነቱን እንደያዘ ከሃያ ሁለት አመት በላይ ቆይቷል። ወያኔ ለአመታት ህዝብን ያታለለባቸዉ የዉሸት ክምሮችና ህዝባዊዉን ትግል ወደ ኋላ ለመጎተት የተጠቀመባቸዉ ስልቶች ዛሬ ሁሉም ሙጥጥ ብለዉ አልቀዉበት ዬኔ ነዉ ብሎ በሚመካበት ትግራይ ዉስጥ ጭምር መግቢያና መዉጪያዉ የጠፋዉ የተከበበ አዉሬ መስሏል። በያዝነዉ የ2006 ዓም ሁለተኛዉ አጋማሽ ወያኔ ጨካኙን የአግአዚ ኃይል እዚህም እዚያም አሰማርቶ ከሚቆጣጠራቸዉ ጥቂት አደባባዮች ዉጭ እንደቀድሞዉ በግልጽ ወጥቶ ወያኔን የሚያሞግስ ወይም የወያኔን የሌለ ገድል የሚናገር ሰዉ የለም። በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ የትግል ስልቶች ወያኔን የሚታገሉ ኃይሎች አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ኃይላቸዉና ቁርጠኝነታቸዉ እየጨመረ መጥቶ ወያኔ ያንን የተለመደ የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዉን እዲወስድና የራሱን የመጨረሻ እሱ እራሱ ሳይወድ በግዱ እንዲያፋጥነዉ እያደረጉት ነዉ።

የአገራችንን አንድነት ሊያላሉና ኢትዮጵያ የሚለዉን ታሪካዊ ስም ከታሪክ ዉጭ ማድረግ ከሚችሉ አደገኛ የወያኔ ባህሪዮች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ዘረኝነቱና ለአገር አንድነትና ዳር ድንበር መከበር ያለዉ የግድየለሽነት ባህሪይ ነዉ። ዛሬ ወያኔ በአራቱም ማዕዘን በየቀኑ እየጨመረና እያየለ የሚሄደዉን የህዝብ ቁጣ ለማብረድና አፋፍ ላይ ለደረሰዉ ስርዐቱ ተጨማሪ ግዜ ለመግዛት የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች ከዚሁ ከዘረኝነት ባህሪይዉ የሚመነጪ እርምጃዎች ናቸዉ። ወያኔ ዕድሜዉ ሊበረክት የሚችለዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነት የሚታገሉ ኃይሎች መግባባት ሲያቅታቸዉ መሆኑን ያዉቃል፤ ስለዚህም በተቻለዉ መጠን ኢትዮጵያዉያንን የሚለያዩና ግጭት ዉስጥ የሚከትቱ አጀንዳዎችን እየፈጠረ ይወረዉርልናናል። ከእነዚህ አገር አጥፊ የወያኔ አጀንዳዎች ዉስጥ አንዱ ህዝብን በዘር ከፋፍሎ እርስ በርሱ እንዲጋጭ ማድረግ ነዉ። ለምሳሌ በቅርቡ ደቡብ ኢትዮጵያ ዲላ ከተማ ዉስጥ በንግዱ ህብረተሰብ ላይ የነጋዴዎችን አቅምና ትርፍ ያላገናዘበ ግብር በመጫን በአንድ በኩል ነጋዴዎቹ በዞኑ አስተዳዳሪዎች ላይ እንዲነሱ በማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ የዞኑ አስተዳዳሪዎች ነጋዴዎቹን የምትሰሙን ከሆነ ስሙን አለዚያ ክልሉን ለቅቃችሁ ሂዱ የሚል አስነዋሪና የዜግነት መብትን የሚጋፋ መልስ እንዲሰጡ በመገፋፋት በጌዲኦ ብሄረሰብና በዲላና አካባቢዉ በብዛት በንግድ ስራ ላይ በተሰማራዉ የጉራጌ ማህበረሰብ መካከል ግጭት እንዲቀሰቀስ ለማድረግ ሞክሯል። ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዉስጥም እንደዚሁ የጋምቤላ ህዝብ ከጋምቤላ ዉጭ ከሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመጡትን ኢትዮጵያዉያን ክልሉ የእናንተ አይደለምና ለቅቃችሁ ዉጡ ብሎ እንዲያስገድድ በመገፋፋት በኢትዮጵያዉያን መካከል ቂምና ጥላቻ እንዲፈጠር አድርጓል። ባለፉት አምስት አመታት ወያኔ ጋምቤላ ዉስጥ ገበሬዉን እያፈናቀለ መሬቱን ለዉጭና ለአገር ዉስጥ በተለይ ለትግራይ ባለኃብቶች በርካሽ ዋጋ ማስረከቡ የሚታወስ ነዉ። ይህ ባዕዳንን ጋምቤላ ላይ እያሰፈረ ኑና እረሱ እያለ የሚለምን ነዉረኛ አገዛዝ ነዉ ዛሬ ኢትዮጵያዉያንን ከጋምቤላ ዉጡ እያለ የሚያስገድደዉ።

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ ምን ያክል እንደተጠላ ለማወቅ ባለፈዉ ቅዳሜ መድረክ አዋሳ ዉስጥ የጠራዉን የተቃዉሞ ሰልፍ መመልከቱ ይበቃል። የአዋሳና የአካባቢዉ ህዝብ በዚህ መድረክ በጠራዉ የተቃዉሞ ሰልፍ ላይ የተገኘዉ ፌዴራል ፖሊስ፤ የክልሉ ፖሊስና የአገዛዙ ካድሬዎች በእያንዳንዱ ሰላማዊ ሰልፍኛ ላይ ያወርዱት የነበረዉን ዛቻ፤ ማስፈራሪያና ና የስድብ ናዳ ከምንም በለመቁጠር ነዉ። በዕለቱ የአካባቢዉን ሰላምና የሰልፈኛዉን ደህንነት አስጠብቃለሁ ብሎ በአዋሳ አደባባዮች ላይ የተሰማራዉ የወያኔ የፖሊስ ኃይል በህግ የተሰጠዉን ኃላፉነት ትቶ ፀረ ህዝብና ፀረ አገር እርምጃዎች ሲወስድ ታይቷል።

ወያኔ ብሶቱን አይቼ 17 ዐመት ታገልኩለት የሚለዉና ዛሬም እወክለዋለሁ ብሎ የሚነግረን ክልል ቢኖር የትግራይ ክልል ነዉ። ዛሬ ትግራይ ዉስጥም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የሞቱት ለዚህ አይደለም ብለዉ ብረት አንስተዉ ወያኔን አምርረዉ የሚታገሉ የትግራይ ወጣቶች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ነዉ። አስራ ሰባት አመት ሙሉ በወያኔ የማይጨበጥ ተስፋ ተታልሎ በከንቱ ህይወቱን የገበረዉ የትግራይ ወጣት ዛሬ እዉነቱ ገብቶት ወያኔን በትግራይ ህዝብ ስም መነገድህን አቁም እያለዉ ነዉ። በቅርቡ በመቀሌና በአካባቢዋ የታየዉ ከፍተኛ ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ወያኔ ለዚህ የሸተተ ስርአቱ ዕድሜ ለመግዛት ቢፍጨረጨርም “ከወደቁ በኋላ መራገጥ ለመላላጥ” ካልሆነ በቀር ካሁን በኋላ ወያኔዎች በስልጣን ላይ መቆየት ቀርቶ የዘረፉትን ኃብት የሚያሸሹበት ግዜም ልንሰጣቸዉ አይገባም።

የወያኔ ጠመንጃና የሚቆጣጠራቸዉ የአፈና ተቋሞች አላናግር ወይም አላስተነፍስ እያሉት እንደ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ አንገቱን ደፍቶ እንዲኖር ስለተገደደ ነዉ እንጂ አመጻኞቹ የወያኔ መሪዎች ለተቀረዉ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ታገልንለት ብለዉ በስሙ ለሚነግዱት የትግራይ ህዝብ በፍጹም የማይበጁ ፀረ አገር ኃይሎች መሆናቸዉን የትግራይ ህዝብ ካወቀ ቆይቷል። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን የትግራይ ህዝብም በቃ በስሜም አትነግዱ ወንድሞቼንና እህቶቼንም አትበድሉ ብሎ ደጋግሞ እየነገራቸዉ ነዉ። ዛሬ ብዙ የትግራይ ወጣቶች እዚያ የዛሬ ሰላሳና ሰላሳ አምስት አመት አባቶቻቸዉ የታገሉበት ጫካ ዉስጥ ገብተዉ እነሱም በተራቸዉ የዛሬዉን ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ በጠመንጃ ጭምር በመፋለም ላይ ይገኛሉ። ወያኔ የመጨረሻ መደበቂያዬ ይሆነኛል ብሎ ይተማመንበት የነበረዉ የትግራይ ክልል ዛሬ ግልጽ በሆነ መልኩ የወያኔን መጨረሻ ለማየት የሚቸኩሉ ጀግኖች ክልል እየሆነ ነዉ።

የትግራይ ጫካዎችን ጨምሮ ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች “ጨርቅ” ብለዉ ያንኳሰሱትን የኢትዮጵያ ባንዲራ በክብር አንግበዉ ከቋጥኝ ቋጥኝ የሚዘልሉት የትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ አርበኞች ወገንን የሚያኮሩ ዘረኞቹን የወያኔ መሪዎች ደግሞ ምነዉ ባልጀመርነዉ የሚያሰኙ የአገርና የወገን አለኝታ ሆነዋል። ዛሬ ወያኔ የትግራይን ምድር የእግር መረማመጃ እስኪጠፋ ድረስ በወታደርና በታንክ ያጠረዉ ይህንኑ በትግራይ ወጣቶች የተገነባ ህዝባዊ የነጻነት ኃይል ስለፈራ ነዉ። አምባገነኖቸ በደም የሚቀባበሉት የተፈጥሮ ባህሪያቸዉ ሆኖ ነዉ እንጂ የታንክና የወታደር ጋጋታ ህዝባዊ ኃይልን የሚያቆም ቢሆን ኖሮ እነሱ ዛሬ ሚኒልክ ቤ/መንግስት ዉስጥ ገብተዉ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊረግጡ ቀርቶ ከተፈጠሩበት ደደቢት በረሃ ስንዝር ሳይራመዱ የእሳት እራት ሆነዉ ይቀሩ ነበር። ወያኔ ዛሬ በምድርና በአየር የታጠቀዉ መሰሪያና ሰራዊት ደርግ ከታጠቀዉ መሳሪያና ከነበረዉ ወታደራዊ ብቃት ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፤ ሆኖም ለነጻነቱ ቆርጦ የቆመን ህዝብ የሚገታ ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል ሰለሌለ ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ድጋፍ አግኝቶ ደርግን መደምሰስ ችሏል። የዛሬዉ አምባገነን ወያኔም ዕድል ከደርግ የተለየ አይደለም። ወያኔ ያሰኘዉን ያክል ቢታጠቅ፤ ያሻዉን ያክል የድንበር አካባቢዎችን በታንክና በወታደር ብዛት ቢያጥር . . . . ደፋርና ጭስ መዉጪያ አያጣምና የወያኔ መሸነፍና መደምሰስ ጉዳይ ቀን እስኪያልፍ ያለፋል ካልሆነ በቀር ያለቀለት ጉዳይ ነዉ።

ደርግ ስልጣን በያዘባቸዉ የመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት ዉስጥ ወታደራዊ አገዛዝ አንቀበልም ብለዉ ደርግን መግቢያና መዉጪያ ካሳጡት የህብረተሰብ ክፍሎች ዉስጥ ትልቁን ሚና የተጫዉተዉ ወጣቱ ትዉልድ ነበር። ይህ ወጣት ትዉልድ በኢትዮጵያ ህዝብ የዲሞክራሲ ትግል ዉስጥ ምን ግዜም ቢሆን ትዝታዉ የማይደበዝዝ አኩሪ የመስዋዕትነት ትግል ያካሄደና ያለምንም ፍርሃት ዉድ ህይወቱን ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነት መከበር አሳልፎ የሰጠ ጀግና ትዉልድ ነዉ። ዛሬም አዲስ አበባ፤ አዋሳ፤ ባህርዳር፤ ጅማ፤ አምቦ ጊምቢና በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተማዎች የሚኖረዉ ወጣት እኔም አገሬም አብረን ከምንጠፋ እኔ ሞቼ አገሬን አኖራለሁ በሚል ኢትዮጵያዊ እልህ ተነሳስቶ የወያኔን የመጨረሻ እያፋጠነ ነዉ። የወያኔን እገድልሃለሁና አጅ እቆርጣለሁ የሚል ዛቻ ከመጤፍ ሳይቆጥሩ በብዕራቸዉ ህዝብን እያስተማሩ ቃሊቲ ከገቡት ጀግኖች ጀምሮ ከተማ ዉስጥ ከወያኔ ጋር መኖር በቃኝ ብለዉ ጠመንጃቸዉን ተሸክመዉ ጫካ እስከገቡት ቆራጥ አርበኞች ድረስ ኢትዮጵያ ዳግም ትንሳኤዋን ለማብሰር የተዘጋጁ እልፍ አዕላፋት ጀግኖች አሏት።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያም መሬቱን ተቀምቶ የተሰደደዉ ወጣት ልክ እንደ ከተማዉ ወጣት በወያኔ ላይ አምርሮ ዱር ቤቴ ብሎ ጫካ ከገባ ቆይቷል። አባቶቹና አያቶቹ ያቆዩለትን መሬት በወያኔ የተቀማዉ የጋምቤላ ገበሬ መሬቴን አለዚያም ህይወቴን ብሎ ወያኔን ማንቀጥቀጥ ከጀመረ አመታት ተቆጥረዋል። የሰሊጥ ማዕከል የሆነዉን ለምለም መሬቱን በወያኔ የተቀማዉና ዛሬም የአባቶቹን አጽም የተሸከመዉን መሬት ለባዕዳን ለመስጠት የሚዶለትበት የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በወያኔ ላይ ጥርስ ከመንከስ አልፎ ቃታ መሳብ ጀምሯል። እነዚህ ከትግራይ እስከ ጋምቤላ ከጋምቤላ እስከ ጎንደር በአራቱም ማዕዘናት የሚታዩ ህዝባዊ አመጾች የሚያሳዩን አንድ ትልቅ ነገር አለ፤እሱም ወያኔ በህዝብ የተጠላ ብቻ ሳይሆን ህዝብ አንቅሮ የተፋዉ ከቆሻሻም ቆሻሻ መሆኑን ነዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዘረኝነት በጉልህ ከሚታይባቸዉና በዘረኝነት ፖሊሲ ላይ ተመስርተዉ ከተዋቀሩ አገራዊ ተቋሞች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የመከላከያ ተቋም ነዉ። የኢዮጵያ መከላከያ ተቋም በተለይ ዋናዉን የዉግያና አገርን የመከላከል ስራ የሚሰራዉ የሰራዊቱ ክፍል የተሰባሰበዉ ከመላዉ የአገሪቱ ክፍሎች ቢሆንም ይህ ተቋም ሁለት ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑና ሆን ተብለዉ የጎደሉ ጉድለቶች አሉበት።አንደኛዉ ጉድለት ሠራዊቱን በተለያየ ደረጃ ከሚመሩና ከሚያዝዙ ወታደራዊ መኮንኖች ዉስጥ ከ95% በላይ የአንድ ዘር ተወላጆች መሆናቸዉ ሲሆን ሁለተኛዉ ትልቅ ጉድለት ደግሞ በኢትዮጵያ ሠራዊት ዉስጥ አግአዚ የሚባል የአዉሬዎች ክምችት የሚገኝበት አንድ ቋንቋ ብቻ የሚናገሩና ከአንድ ክልል የመጡ ተዋጊዎች ያሉበት ሠራዊት መኖሩ ነዉ። የአገሬን አንድነትና ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ፈንጂ አምካኝ የነበሩ ወታደሮች ከገዢዉ ፓርቲ ብሄር ባለመወለዳችን አድሎ ተፈጽሞብናል አሉ

ከ1991 እስከ 1992 በተካሄደዉ የኢትየጲያና የኤርትራ ጦርነት ወቅት በፈንጂ ማምከን ስራ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩ ወታደሮች በቋንቋና በዘር እየተለየን አገልግሎታችንን በሚመጥንና እስከዛሬ ከፈልነውን መስዋትነት ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ከሳ ሳይከፈለን ከመከላከያ እንድንሰናበት ተደርገናል ብለዋል።

ሰሞኑን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ብርጋዲየር ጄኔራል ተክለብርሃን ወ/ዓረጋይ ወደ አማራ፣ ኦሮምያና ደቡብ ክልሎች ተዘዋውረው ወታደሮችን ያነጋገሩ ሲሆን "ጊዜው ለልማት እና ለስራ የሚነሳሱበት እንጅ አድማ በመምታት ነገር የሚያሰሩበት አይደለም" በማለት አስጠንቅቀዋቸዋል።

"የግፍ ግፍ ተፈፅሞብናል" ያሉት ፈንጅ አምካኝ ወታደሮች፣ ከፍተኛ መስዋትነት የከፈልነው የአማራ ኦሮሞ እና ደቡብ ብሄር ተወላጆች ከስራ እየተሰናበትን የህወሃት አባላት አዲስ ምልምል ወታደሮች የስራ እድል እየተሰጣቸው ነው በማለት በተለይ በሰላም አስከባሪ ስም እየተፈጸመ ያለውን አድልዎ በማንሳት ተቃውሞቸውን አሰምተዋል። 200 የሚደርሱ በአባይ ግድብ ተቀጥረው እንዲሰሩ የተደረጉ ፈንጅ አምካኞች "አታስፈልጉም" ተብለው መባረራቸውንም አውስተዋል።በሶስቱ ክልሎች መስዋትነት ከፍለን በብሄራችን የተነሳ ከስራ ተባረርን የሚሉ 513 ፈንጅ አምካኝ ወታደሮች አሉ። ከደህንነት ክፍል የተገኙው መረጃ እንደሚያሳየው መንግስት የሶስቱ ክልል ፈንጅ አምካኝ ተወላጅ ወታደሮች ላይ ጥብቅ ስለላ እና ክትትል የሚያደርግ ሲሆን፣ ከድተው በትጥቅ ትግል የሚታገሉትን ተቃዋሚዎች ሊቀላቀሉ ይችላሉ የሚል ስጋት አለው።

## መድረክ አዋሳ ላይ ሙብት ለማስከበር የጠራው የታቃዉሞ ሙብት የጣሰ እንደነበር ተነገረ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መድረክና አባል ድርጅቶቹ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)፣ የኢትዮጵያ ማኅበረ ዲሞክራሲ ደቡብ ኅብረት አንድነት ፓርቲ በህብረት አዋሳ ላይ የጠሩት የተቃዉሞ ሰልፍ ብዙ ህዝብ የተሳተፈበት ቢሆንም የተለመደዉ የወያኔ እንግልት፤ ድብደባና ማስፈራሪያ ያልተለየዉ እንደነበር ደቡብ ኢትዮጲያ ዉስጥ የሚገኙ ዘገቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ "ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ተቃውሞዎችን በኃይል ማፈን ይቁም" በሚል ባለፈዉ ቅዳሜ ሰኔ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. አዋሳ ዉስጥ የተጠራዉ ሰላማዊ ሠልፍ በሰላም ተጀምሮ በሰለም ተጠናቅቋል ያሉት የፓርቲው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጥላሁን እንደሻው፣ ወያኔ ሕዝቡ ወደ ሠልፉ እንዳይወጣ የተለያዩ ማነቆዎችን ፈጥሮ ሰልፉን ለማጨናገፍ ሲሞክር ዉሏል ብለዋል። አቶ ጥላሁን ንግግራቸዉን በመቀጠል ቅዳሜ ለሚካሄደዉ ሰልፍ ወያኔ የዕውቅና ደብዳቤ የሰጠን ሐሙስ 11 ሰዓት ላይ ነው፤» በማለት ገዥው ፓርቲን የኮነኑ ሲሆን፣ ቢሆንም ግን ሕዝቡ ይህን አፈና ተቋቁሞ በመውጣት የተሳካ ሠልፍ አካሂደናል ብለዋል።

በሰልፉ ላይ መድረክ አገሪየቱ ዋና ዋና ችግሮች ናቸዉ ያላቸዉን መሠረታዊ ችግሮችና በሕገ መንግሥቱ ተደንግገው ነገር ግን ወያኔ ተግባራዊ ያላደረጋቸዉን ወይም የሚጥሳቸዉን ህጎች ለሕዝብ አቅርቧል። ፓርቲው በዝርዝር ካስቀመጣቸው ነጥቦች መካከል የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት ጉዳይ፤ የመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲ በትክክል ሥራ ላይ አለማዋል፤ ፍትሃዊ የምርጫ ቦርድ አለመኖርና ሰለማዊ ዜጎችን ሽብርተኛ እያሉ ማስር ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። ከዚህ በተጨማሪም ፓርቲው ለዘረዘራቸው ችግሮች መፍትሔ ያላቸውን ሐሳቦች ያቀረበ መሆኑን፣ ከእነዚህም ውስጥ ለትክክለኛ የመድበለ ፓርቲና ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ተግባራዊነት፣ ለተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃና ሕጋዊ እንቅስቃሴዎችና ነፃ የውድድር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ በዜጐች መካከል የሚደረግ የፖለቲካዊ ወገንተኝነት አሠራር እንዲቆምና ፍትሐዊና እኩልነት የሰፈነበት አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀና የፓርቲዎችን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ገለልተኛ የምርጫ ቦርድና ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎችን ያካተተ የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ እንዲኖርና በትክክል ተግባራዊ ማድረግና ለፖለቲካ ፓርቲዎች የመንግሥትን የድጋፍ ገንዘብ በእኩልነትና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲያገኙ ማድረግ የሚሉት ይጠቀሳሉ። ይህ በሐዋሳ የተካሄደው ሠልፍ አዲስ አበባ ላይ ተደርጐ ከነበረው ሠልፍ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ እንዳለው የገለጹት አቶ ጥላሁን፣ በቀጣይም በሌሎች ከተሞች ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሠልፎች እንደሚካሄዱም አክለው ገልጸዋል።

## ወያኔ ባሰራቸዉ ጋዜጠኞችና ጦማሪያን ላይ ማስርጃ ማቅረብ እንዳቃተዉ የተጠርጣሪዎቹ ጠበቃ አሳወቁ

የወያኔ ፖሊስና ደህንነት መስሪያ ቤቶች ጋዜጠኞችንና ጦማሪያንን በሽብርተኝነት ጠርጥረው ከሃምሳ ቀናት በላይ ካሰሩ በኋላ አሁንም ይህ ነዉ የሚባል ማስረጃ ማግኘት አለመቻላቸዉ  የሚያሳየዉ ወያኔ ዜጎችን ያለማስረጃ አስሮ ማስረጃ እንደሚፈበርክ ነዉ ሲሉ ተጠርጥረዉ በእስር የሚሰቃዩት ጋዜጠኞችና ጠበቃ አስታወቁ። የተጠርጣሪዎቹ ጠበቃ የሆኑት አቶ አመሐ መኰንን ይህንን ያስታወቁት ሰኔ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. ለአራተኛ ጊዜ በፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ወንጀል ችሎት ቀርበው በነበረበት ወቅት ነበር።

ጠበቃ አመኃ መኰንን ከዚህ በተጨማሪ ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ሥር ውለው ማዕከላዊ እስር ቤት በቆዩባቸው 50 ቀናት ውስጥ አራት ጊዜ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ፣ የተጠርጣሪዎቹ ቤተሰቦች የሆኑ ብቻ ሁለት ሁለት ሰዎች ችሎቱን እንዲታደሙ የተደረገ ቢሆንም፣ ሰኔ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. በዋለዉ ችሎት ግን ማንም ሰው ወደ ችሎት እንዳይገባ ተከልክሏል በማለት በፍርድ ቤቱ ላይ አማርረዋል።

ሰኔ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. የዋለዉ ችሎት ከተዘጋ በኋላ ጠበቃ አመኃ መኰንን ከፍርድ ቤቱ ዉጭ ይጠብቃቸዉ ለነበረ የተጠርጣሪዎቹ ቤተሰብና ጓደኛ በሰጡት ጥያቄና መልስ፤ "ፖሊስ ምንም አዲስ ነገር አላቀረበም" ካሉ በኋላ፣ ባለፉት 28 ቀናት ውስጥ ምን ምን ሥራዎችን እንደሠራ ፍርድ ቤቱ ጠይቆት የተወሰኑ የትርጉም ሥራዎችን እንዳሠራ፣ የተወሰኑ የባንክ ማስረጃዎችን እንዳገኘ፣ የተወሰኑ የቴክኒክና ሌሎች በርካታ ሥራዎችን መሥራቱን እንዳስረዳ ገልጸዋል። በርካታ ሥራዎች የሠራ ቢሆንም ከሥራው ውስብስብነትና ስፋት አንፃር በርካታ ሥራዎች እንደሚቀሩት በመግለጽ፣ ለተጨማሪ ምርመራ 28 ቀናት እንዲፈቀድለት ፍርድ ቤቱን መጠየቁን አቶ አመሐ ተናግረዋል።

መርማሪ ፖሊስ "በርካታ ሥራዎች" በማለት በጥቅል የተናገረውን በሚመለከት የሠራውንና ያልሠራውን አንድ ሁለት ብሎ እንዲያስረዳ ፍርድ ቤቱ እንዳዘዘው የገለጹት ጠበቃው፣ የተወሰኑትን የምስክሮች ቃል ተቀብሎ የተወሰኑትን መቀበል እንደሚቀረው፣ ተባባሪዎች ወደ ክልል በመሄዳቸው የምርመራ አባላትን ልኮ እየተጠባበቀ መሆኑን፣ አዲስ አበባ ውስጥም ያልያዛቸው ተባባሪዎች እንዳሉና ለመያዝ እየሠራ መሆኑን፣ የተወሰነ ሰነድ ማስተርጐም እንደሚቀረው አስረድቶ የጠየቀው ጊዜ እንዲፈቀድለት በድጋሚ መጠየቁን አስረድተዋል።

ጠበቃ አመሐ በበኩላቸው፣ መርማሪ ፖሊሶቹ ያቀረቡትን ሪፖርት በመቃወም መከራከራቸውን ተናግረዋል። ተጠርጣሪ ደንበኞቻቸው ከታሰሩ 50 ቀናት እንዳለፋቸው፣ አራት ጊዜ ፍርድ ቤት ቀርበው ጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸው እንደተፈቀደ፣ የፈለገ ውስብስብ ወንጀል ቢሆን እንኳን ከተያዙ ጊዜ ጀምሮ ምርመራ ቢጀመር 50 ቀናት ምርመራ ለማጠናቀቅ በቂ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ማስረዳታቸውን ገልጸዋል። ይኼ የሚያሳየው ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹን የያዛቸው ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይኖረው መሆኑን ነው፤ ያሉት ጠበቃ አመሐ፣ ተጠርጣሪዎቹን ዋጋ እያስከፈላቸውና ሕግን የጣሰ ተግባር በመሆኑ የመርማሪ ፖሊስን የምርመራ ውጤት ፍርድ ቤቱ ሊቀበለው እንደማይገባ በመናገር መከራከራቸውን አብራርተዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የመጨረሻዉ መጀመሪያ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ዳር ድንበር አስከብራለሁ ብሎ ከተለያዩ አካባቢዎች የተሰባሰበዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት በዘር ተከፋፍሎ የወያኔ መጠቀሚያ መሆን ሰልችቶታል።በተለይ ይህ ሰራዊት ብዛቱን በሚመጥን ቁጥር የመሪነትና የአዛዥነት ቦታ ስለማይሰጠዉ ሁል ግዜ በሚንቁትና በሚያንቋሽሹት የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መመራት አንገሽግሾታል። ዛሬ በየበረሃዉ ለሚገኙት የነጻነት አርበኞች እባካችሁ እንገናኝና አገራችንን አንድ ላይ ሆነን ነጻ እናዉጣ የሚል የትግል ጥሪ በተደጋጋሚ የሚመጣዉ ከዚሁ በዘረኝነት አለንጋ ከሚገረፈዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነዉ። ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ በተለይ ባለፉትሦስት አመታት በኢትዮጵያ ሠራዊት ዉስጥ ትልቁ የመወያያ አርዕስት አንዴት አድርገን የነጻነት እበኞችን እንቀላቀል የሚለዉ ጥያቄ ነዉ። በሠራዊቱ ዉስጥ ሆኖ በዚህ አርዕስት ላይ የማይወያይ የሰራዊቱ አባል ቢኖር እንደ ዘይትና ዉኃ ቅልቅል በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ ባዕድ አካል ሆኖ የሚታየዉ አዉሬዉ የአግአዚ ሠራዊት ብቻ ነዉ። አግአዚ ደግሞ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሳይሆን በኢትዮጵያ ሰራዊት ዉስጥ እንደ እንክርዳድ የበቀለ ፍጹም ባዕድና ጨካኝ የሆነ የወያኔ መገልገያ ነዉ።

ከዚህ በላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነዉ ወጣቱ፤ ገበሬዉ፤ ነጋዴዉ፤ ከተሜዉና ወታደሩ ሁሉም ወያኔን የሚቃወም ብቻ ሳይሆን ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን ለመደምሰስ የተዘጋጁ `ኃይሎች ናቸዉ። ባለፈዉ ግንቦት ወር ወያኔ ዘረኝነትንና ሙሰኝነትን ኢትዮጵያ ዉስጥ የተከለበትን ሃያ ሦስተኛ አመት ሲያከብር የኢትዮጵያ ህዝብ የተዋርድንበትን ቀን አናከብርም ብሎ ወያኔ የራሱን በዐል ብቻዉን አክብሮ ዉሏል። ከዚህ በተጨማሪ እጅግ በጣም ብዙ ኢትዮጵያዉያን ይህንን የባርነት ቀን እንደገና ሲከበር ማየት አንደማይፈልጉ በይፋ ተናግረዋል። በእርግጥም ካሁን በኋላ ወያኔ ግንቦት ሃያን ብቻዉንም ቢሆን እንዲያከብር መፍቀድ የለብንም። ደግሞም ወደድንም ጠላን ወይም አወቅን አላወቅን ወያኔ ግንቦት ሃያን የሚያከብረዉ ብቻ ሳይሆን እንዳሰኘዉ ረግጦ የሚገዛን እኛ አሜን ብለን ስለፈቀድንለት ብቻ ነዉ። ህዝብ በአንድ ድምጽ አልገዛም ብሎ አለመገዛቱን የሚያሳይ እርምጃ መዉሰድ ቢጀምር አይደለም በዐል ማክበር ወያኔዎች ሰኞ ያደሩበት ሚኒልክ ቤ/መንግስት ዉስጥ ማክሰኞ ማምሸትም አይችሉም ነበር።

መሬት አልባዉ የኢትዮጵያ ገበሬ ወያኔ እስካለ ድረስ ልጆቼን ብሎ ስለወደፊቱ ማሰብ ቀርቶ የዕለት ጉርሱን የማግኘት ዋስትናም የለዉም። ነጋዴዉም እንደዚሁ ነዉ። ለወያኔ ሙሰኞች ካላጎበደደና ግማሽ ትርፉን ለእነሱ ካልገበረ ነግዶ መኖር ቀርቶ በልቶ ማደር የማይችልበት ግዜ እየመጣ ነዉ። ከተሜዉ ኢትዮጵያዊስ ቢሆን እስከመቼ ነዉ ሰላማዊ ልጆቹ ከጉያዉ እየተጎተቱ ሽብርተኞች ተብለዉ ዕድሜ ልክ ተፈርዶባቸዉ ቃሊቲ ሲገቡ የሚመለከተዉ? እስከመቼ ነዉ ዬት ገቡ ተብለዉ አድራሻቸዉ የጠፋ ልጆቹ መንገድና ህንጻ ሲሰራ የጅምላ መቃብራቸዉ በግሬደር እየተቆፈረ ሲወጣ የሚመለከተዉ? ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጡት የመከላከያና ፖሊስ ሠራዊት አባላት እስከመቼ ነዉ እነሱ እራሳቸዉ በወያኔ ዘረኝነት እየተለበለቡ ለወያኔ ዕድሜ መራዘም ሲሉ ወንድሞቻቸዉንናነ እህቶቻቸዉን የሚገርፉትና የሚያዋርዱት?

ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ገዳማትን የእርሻ ቦታ አድርጓቸዋል፤ የእምነት ተቋሞችን የከፋቱ መሠረት አድርጓቸዋል፡ ምሁራንን ደግሞ አገራቸዉን ጥለዉ እንዲሰደዱ አድርጓል። ባጠቃላይ ወያኔ ያልበደለዉ፤ ያላሳቀቀዉ ወይም ተስፋዉን ያላጨለመበት የህብረተሰብ ክፍል የለም። የገበሬዉ፤ የከተሜዉ፤ የነጋዴዉ፤ የወታደሩ ፤ የወጣቱና የምሁሩ ጠላት ወያኔ መሆኑን ካወቅን ዉለን አድረናል፤ ታዲያ ለምንድነዉ ይህንን የጋራ ጠላት በገራ የማናስወግደዉ? ከዛሬ በኋላ ወያኔ ስልጣን እንደያዘ በሚቆይባት በእያንዳንዷ ቀን የእኛ ስቃይና መከራ መብዛቱ ብቻ ሳይሆን ጥፋቱም የኛ መሆኑን አጥብቀን ልንረዳ ይገባል። ወያኔ እንደሆነ ቀንበር ለመሸከም የተመቻቸ ትከሻ ካገኘ ምን ግዜም ቢሆን ከመግዛት፤ ከማሰርና ከመግደል ወደ ኋላ አይልም። አልገዛም፤ አልታሰርም ወይም አትገድሉኝም ብሎ በወያኔ ላይ መነሳት የዚህ ትዉልድ ኢትዮጵያዉያን ሀላፊነት ነዉ፤ ይህ ሀላፊነት ደግም በህብረት ቆመን ለአንድ አላማ በአንድነት ከታገልን በቀላሉ ልንወጣዉ የምንችለዉ ሀላፊነት ነዉ። ሰለዚህ የዛሬም ጥሪ እንደትናንቱ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወያኔን ለማስወገድ ሀላፊነቱን ይወጣ የሚል ነዉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!**

## የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎች የፍትህ ያለህ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዘጋቢያችን በዞኑ አንዳንድ ከተሞች ጭምር ተዟዙሮ የቃረመው መረጃም እንደሚያመለክተው በዞኑ ህዝቡ በጉጅሌው ወያኔ አስተዳደር እጅግ መማረሩንና በተለይም ወጣቱ ክፍል በአገዛዙ እየደረሰበት ባለው በደል እጅግ በመማረር አካባቢውን ጥሎ በመሸሽ ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ጉዳዩን በማስመልከት መረጃ ያደረሰን የውስጥ ምንጫችን እንዳመለከተው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝና ሹማምንቱ በጡንቻቸው ስለሚያሰቡ ህዝቡን ለስቃይ፤ ወጣቱን ለስደት ዳርገውታል በማለት በተለይም በዞኑ ከተሞች እየተስተዋለ ያለውን ችግር ገልጾወታል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በቤት አፍራሽ ግብረ ሃይሉ አማካኝነት በደብረ ማርቆስ ከተማ ከ500 በላይ ህጋዊ ቤቶችን በጉልበት በማፍረሱ በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ጎዳና ላይ መበተናቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

ባሳለፍነው ሳምንት አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ በደብረ ማርቆስ ከተማ "የሚሊዮኖች ድምጽ ለመሬት ነጻነት" የሚለው ዘመቻው አካል የሆነ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጉና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች በነቂስ በመውጣት በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ የገለፁበት እንደነበርም መዘገቡ ይታወሳል።